ምንኩስና በኢትዮጵያ

ክ4ኛው መ/ክ/ዘ በፊት

ሥርዓተ ምንኩስና ወደ ሀገራችን የገባው በኢትዮጵያ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ በአባ ጳኩሚስ ዘመን ቢሆንም የብሕትውና ኑሮ ግን በሀገራችን ከዚያም ቀድሞ እንደነበረ የሚጠቁሙ አንዳንድ መረጃዎች አሉ፡፡

አባ አምንዮስ ሥርዓተ ምንኩስና ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት አሞንዮስ የተባሉ ባሕታዊ በተንቤን ቆላ ደብረ አንጣ በተባለው በረሃ በጾም በጸሎት ተወስነው ይኖሩ ነበር፡፡

አባ ዮሐኒ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ በትግራይ ተንቤን አውራጃ በሀገረ ሰላም ቀበሌ ተወለዱ፡፡ በዚያን ዘመን ሥርዓተ ምንኩስና ወደ ኢትዮጵያ ባይገባም አበው በምናኔ በበረሃ ይኖሩ ነበር፡፡ የአባ ዮሐኒ ቤተሰቦች ድሆች ስለነበሩ አባ አሞንዮስ ወስደው አሳደጓቸው፡፡ ካደጉ በኋላም ከአባ አሞንዮስ ተለይተው ወደ በረሃ ለብቻቸው በመውረድ በተጋድሎ ሲኖሩ ከቆዩ በኋላ በተወለዱ በ30 ዓመታቸው ጎንደር 5 ቀን እግዚአብሔር ወደ ብሔረ ሕያዋን በመላእክት እጅ እንደወሰዳቸው ገድለ አባ ዮሐኒ ይገልጣል፡፡

ሥርዓተ ምንኩስና በኢትዮጵያ ለመስፋፋት የበቃው በሁለት ዓይነት መንገድ ነው፡፡

ከውጭ ወደ ሀገራችን በገቡ ቅዱሳን

በኢትዮጵያውያን ቅዱሳን

ወደ ሀገራችን የገቡ ቅዱሳን፡

ከመካከለኛው ምሥራቅ፣ ከታናሽ እስያና ከሮማ ግዛት ወደ ሀገራችን በልዩ ልዩ ምክንያት ገብተው ሥርዓተ ምንኩስናን ያስፋፉ ገዳማትን የገደሙ አበው አያሌ ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

አባ ሊባኖስ

በቁስጥንጥንያ አጠገብ ሩም በተባለች ቀበሌ ተወለደ፡፡ በልጅነቱ በዲቁና ሲያገለግል ቆይቶ ወደ ግብፅ በመምጣት ሥርዓተ ምንኩስና ተፈጸመለት፡፡ ወደ እስክንድርያ በመጓዝም እስከ ቁምስና ማዕረግ የደረሰ አባት ነው፡፡ በ486 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት 80 ዋሻዎች አንፆ ሥርዓተ ምንኩስናን አስፋፍቶ በዐፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት ጥር 3 ዐርፏል፡፡

ተሰዐቱ ቅዱሳን

በኬልቄዶን ጉባዔ የልዮን ጦማር ያልተስማሙትን ኦርቶዶክሳውያን አባቶች ሮማውያን በግፍ በሚያሳድዱበት ዘመን ከሮም፣ ከታናሽ እስያና ከመካከለኛው ምሥራቅ ወደ ግብፅ በመውረድ በዚያም ሥርዓተ ምንኵስናን ፈጽመው፣ ተምረው፣ በአንድነት በ480 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ሥርዓተ ምንኵስናን የበለጠ ያስፋፉ አበው ናቸው። ገዳማቱ እስከዛሬ ድረስ ይገኛሉ። እነዚህ ዘጠኝ ቅዱሳንም የሚከተሉት ናቸው።

ስም	ገዳም	የዕረፍት ቀን	ሀገራቸው
አባ አሴፍ	ብንዛን (አህስአ)	መጋቢት 11	ቂሣርያ
አባ አረጋዊ	ደብረ ዳሞ	ጥቅምት 14	ሮም
አባ አፍጼ	የሃ/ዬሐ	ግንቦት 12	እስያ
አባ ሊቃኖስ	ደብረ ቆናጽል	ኀዳር 21	ቁስጥንጥንያ
አባ ገሪማ	መዱራ	ሰኔ 29	ሮም
አባ ጉባ	ገርዓልታ	ግንቦት 29	ኪልቂያ
አባ ይምዓታ	ገርርዓልታ	ጥቅምት 23	ቆሲያ
አባ ጸንጠሌዎን	አኵስም (አጠገብ)	ጥቅምት 6	ሮም
አባ ጽሕማ	ጼዼንያ	ጥር 16	አንጾኪያ

አባ ዮሐንስ (ዘጉንድ ተ/ሃይማኖት)

የትውልድ ሀገራቸው ፍልስጥኤም ሲሆን ወደ ኢትዮጵያ የገቡት በ1100 ዓ.ም. ነው። አባ ዮሐንስ በተለይ ከአፋር ክልል ደብረ አዘሎ፣ ደብረ ደንኖ፣ ደብረ ፀገ፣ ደብረ ገሮ፣ ደብረ አሳራ በተባሉ ሥፍራዎች ሥርዓተ ምንኵስናን አስፋፍተዋል። በመጨረሻም በለሳ በረሃ ወርደው ጉንድ ገዳምን በመመሥረት ሐምሌ 29 ቀን በተወለዱ በ500 ዓመታቸው በ1500 ዓ.ም. ዐርፈዋል።

ጻድቃን

ተሰዐቱ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣታቸው በፊት በግልና በኀብረት እየሆኑ አያሌ መነኰሳት ወደ ሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ገብተው ነበር። እነዚህም ቅዱሳን (ጻድቃን) እየተባሉ ሲሆን በቅርቡ መጽሐፈ ገድላቸው እስከ ተገኘበት ጊዜ ድረስ ስለነርሱ የሚታወቀው እጅግ ጥቂት ነበር። እነርሱም በኤርትራ ቆላማው ሥፍራ ሥርዓተ ምንኵስናን ያስፋፉ መሆናቸው ታውቋል።

አርባ ሐራዊ

አቡነ ሐራ የተባሉት ቅዱስ በዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ በመግባት በአኵስም ከቆዩ በኋላ አያሌ መጻሕፍት እና ንዋያተ ቅድሳት ይዘው ወደ መንዝ ማማ ምድር በመምጣት በዋሻ ውስጥ ተቀመጡ፡፡ የዮዲት ዘመን ካለፈ በኋላ ደግሞ 40 ቅዱሳን ከግብፅ ከገዳመ አስቄጥስ መጥተው ከአቡነ ሐራ ጋር 4 ሰዓት የሚያስኬድ ዋሻ ፈልፍለው ማኅበረ መነኰሳት አቁመው መኖር ጀመሩ፡፡ ከዚህም መካከል 20ዎቹ ዞረው ሲያስተምሩ 20ዎቹ ደግሞ የተግባር ቤቱን ሥራ ያከናወኑ ነበር፡፡

በአካባቢውም ትምህርተ ወንጌልንና ሥርዓተ ምንኵስናን ካስፋፉ በኋላ አስቀድመው 40ው ቅዱሳን በኋላም አቡነ ሐራ በተወለዱ በ220 ዓመታቸው በ1100 ዓ/ም ዐረፉ፡፡ የእርሳቸውንም ፈለግ አባ ፍሬ ሠናይ የተባሉ አባት ተከተሏቸው፡፡ ይህም ሥፍራ ዛሬ አርባራ መድኃኔዓለም ገዳም በመባል ይታወቃል፡

በአሁኑ ወቅት ይህ ቦታ በተለያየ አፅፍ የተከፈኑ እና የተገነዙበትም ማሠሪያ ክር በእጃቸውና በእግራቸው ጣት ላይ የሚታይ ብዙ አፅሞች ይገኙበታል፡፡ ምንም እንኳን ዋሻው በአፅም የተሞላ ቢሆንም ከአካባቢው የሚወጣው መዓዛ ግን ከሙታን መንደር የሚገኝ መጥፎ ሽታ ሳይሆን (አልባብ አልባባ) የሚል መልካም መዓዛ ነው፡፡

የአካባቢው አረጋውያን እንደሚናገሩት ከሆነ ከኢጣሊያ ፋሺስት ወረራ በፊት ዘወትር የማኅሌት÷የከበሮና የዕልልታ ድምፅ ይሰማበት ነበረ፡፡ በተጨማሪም እጅግ ግዙፍ የሆነ ነጭ አሞራ እየበረረ ወደ ዋሻው ሲገባ ማየት የዘወትር ክስተት ነበረ፡፡ ከዚያ ወዲህ ግን ይህ ነገር ብዙም አይታይም፡፡

ቦታውን ከአካባቢው ምእመናን ጋር የሚያገናኘው ሌላው ነገር ደግሞ መሬት ሰብል እንዳትሰጥ ሰብል አጥፊ ተባይ ሲነሣ፣ እንስሳቱ ወተት መስጠታቸውን ሲቀንሱ ገበሬዎቹ አፅሞቹ ካረፉበት ቦታ አፈሩን በመዝገን በማሳቸው ላይ ይበትናሉ፤ እንስሳቱንም ያሻሽበታል፡፡ እንደ እምነታቸውም እንደሚያደርግላቸው በየዓመቱ ጥር 13 ቀን የሚገባው የእንስሳትና የሰብል ውጤት ምሥክር ነው፡፡ ከዋሻው የሚወጣው መልካም መዓዛም አሁንም ያልተቀየረ መሆኑን ዜዶ የሚመለከት ምሥክር ነው፡፡

አባ ኖብ

ትውልዳቸው በሶሪያ ሲሆን ወደ ኢትዮጵያ ወጥተው ከአቡነ ሳሙኤል ዘዋልድባ ጋር ተገናኙ፡፡ የኢትዮጵያውያንን ቋንቋና ባሕል ካጠኑ በኋላ በትግራይ ተንቤን ፀፀራ ወረዳ ከሚገኘው ዋሻ ላይ ቤተ ክርስቲያን ተክለው ገዳም መሠረቱ፡፡ ከዚያም ቀጥለው በመላ ኢትዮጵያ በመዘዋወር ገዳማትን መሥርተው በ1100 ዓ.ም. ኅዳር 8 ቀን ዐረፉ፡፡

ትውልዳቸው በግብፅ ሲሆን ገና በሕፃንነታቸው በልዑል እግዚአብሔር ፈቃድ በ1100 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ሥርዓተ ምንኩስናን ያስፋፉ አባት ናቸው። እግዚአብሔር በሰጣቸው የ562 ዓመት ዕድሜ አያሌ ገዳማትን የገደሙ ሲሆን በተለይም የዝቋላና የምድረ ከብድ ገዳማት እስከዛሬ የፀኑ ናቸው።

በኢትዮጵያ የምንኩስናና የገዳማት ታሪክ ውስጥ ከ3ኛው - 12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያለው ጊዜ በአብዛኛው ከውጭ በመጡ አበው ሥርዓተ ምንኩስና የተስፋፋበት ሲሆን ከ12ኛው-15ኛው ያለው ደግሞ ከመላ ኢትዮጵያ በተነሡ አበው ቅዱሳን ሥርዓተ ምንኩስናና የገዳማት ትክል ከሰሜን ወደ ምዕራብ፣ ምሥራቅና ደቡብ የተስፋፋበት ወቅት ነው።

ምንጭ

1. ትንሣኤ ቁ.99/1978
2. ገድለ አባ ሊባኖስ
3. ገድለ አባ ዮሐንስ
4. ዜና መንዝ
5. የአንኰበር መሳፍንት የታሪክ መጽሐፍ
6. ትንሣኤ ቁ.11/79
7. ትንሣኤ ቁ.22/80
8. Conti Rossini, steria PL.XLIV
9. ሉሌ መላኩ፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አ.አ 1986
10. አባ ጎርጎርዮስ፤ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ
11. አባ ጎርጎርዮስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ